**מדינת ישראל**
**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות לבתי ספר על־יסודיים
מועד הבחינה: קיץ תשע"ו, 2016
מספר השאלון: 572381

# אמהרית

## על פי תכנית הרפורמה ללמידה משמעותית

## הוראות לנבחן

א. משך הבחינה: שלוש שעות.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה: בשאלון זה חמישה פרקים.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | קטע שנלמד | — | 30 נקודות |
| פרק שני | — | לשון | — | 20 נקודות |
| פרק שלישי | — | קטע שלא נלמד | — | 25 נקודות |
| פרק רביעי | — | קטע שנלמד | — | 25 נקודות |
| | | סה"כ | — | 100 נקודות |

ג. חומר עזר מותר בשימוש: אין.

ד. הוראות מיוחדות: (1) כְּתֹב את כל התשובות בשאלון עצמו (במקומות המתאימים).
(2) כְּתֹב את כל התשובות באמהרית ובעט בלבד. אסור למחוק בטיפקס.
(3) בסיום הבחינה החזר את השאלון למשגיח.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

/በሚከተለው ገጽ ላይ ይቀጥላል/

| | |
|---|---|
| አስተውል! መልሶችህን በግልፅና በትልልቅ ፊደሎች በእስክርቢቶ ብቻ ጻፍ። | שים לב: את התשובות כְּתוֹב בָּרוּר, בעֵט (ולא בעיפרון) ובאותיות גדולות. |

## ክፍል አንድ – የተማሩት ምንባብ

(30 ነጥብ)

ከታች የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች **በሙሉ** መልስ።

## פרק ראשון – קטע שנלמד

(30 נקודות)

קרא את הקטע שלפניך, וענה על כל השאלות 1-10 שאחריו.

## የኤሊና የጥንቸል ውድድር

ኤሊ በጣም ቀሰስተኛ ፍጡር ናት። ምክንያቱም ሰውነቷ ድንጋይ በሚመስል ቆዳ ስለተሸፈነ ነው። በተቃራኒው ደግሞ ጥንቸል ፈጣን ናት። ከፍጥነቷ የተነሳ፣ ውሻ እንኳን፣ በአጭር ርቀት አይደርስባትም።

አንድ ቀን ኤሊ ወደቤቷ ስትሄድ፣ ጥንቸልን መንገድ ላይ አገኘቻት። ኤሊም እንደልማዷ በጣም ቀስ እያለች ትሄድ ነበር። ጥንቸልዋም ኤሊን ስታያት "አንቺ ቀርፋፋ! ወዴት እየሄድሽ ነው?" አለቻት። ኤሊም ተናደደችና "ለምን ቀርፋፋ ትዪኛለሽ? ከፈለግሽ ነይ በሩጫ እንወዳደር" አለቻት። ጥንቸልዋም "እሺ" አለች።

በሩጫው ቦታ ከተስማሙ በኋላም ቀበሮን የውድድሩ ዳኛ አደረጉት። ቀበሮም "አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት" አለና ሩጫው ተጀመረ። ጥንቸልዋም ኤሊን ወዲያው ቀደመቻት። ኤሊ ግን በጣም ወደኋላ ቀረች። ጥንቸልዋም ኤሊን ለመጠበቅ እሣር ላይ ጋደም አለች። በዚህን ጊዜ እንቅልፍ ወሰዳት። ኤሊም ቀስ እያለች በመሄድ፣ እውድድሩ መጨረሻ መስመር ላይ ደረሰች። ተመልካቾች ለኤሊ ሲያጨበጭቡላት ሰምታ ጥንቸልዋ ከእንቅልፏ ነቃች። በጣምም ተናደደች። ጥንቸልዋም መሸነፏን አወቀች እና ኤሊን "ሁለተኛ አልሰድብሽም" አለቻት።

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

لا تكتب في هذه المنطقة
לא לכתוב באזור זה

לא לכתוב באזור זה
لا تكتب في هذه المنطقة

**ጥያቄዎች** (30 ነጥብ)

በምንባቡ መሠረት ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ መልስ። (እያንዳንዱ ጥያቄ 3 ነጥብ ይይዛል በአጠቃላይ 30 ነጥብ)

**השאלות** (30 נקודות)

ענה על השאלות 10-1 באמהרית, לפי הקטע.
(לכל תשובה נכונה — 3 נקודות;
סה"כ — 30 נקודות)

1. ኤሊ ቀሰስተኛ የሆነችው ለምንድን ነው?

2. ውሻ ጥንቸልን በአጭር ርቀት የማይደርስባት ለምንድን ነው?

3. ኤሊ ወዴት ስትሄድ ነው ጥንቸልን ያገኘቻት?

4. ጥንቸል ኤሊን ስታያት ምን አለቻት?

5. ኤሊ ለጥንቸሏ ምን ብላ መለሰችላት?

6. ኤሊና ጥንቸል፣ በምን ከተስማሙ በኋላ ነው ቀበሮን የውድድሩ ዳኛ ያደረጉት?

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

7. ቀበሮ ምን አለና ነው ሩጫው የተጀመረው?

8. ጥንቸል እሣር ላይ ለምን ጋደም አለች?

9. ጥንቸል ከእንቅልፏ መቼ ነቃች?

10. ጥንቸሏ መሸነፏን ባወቀች ጊዜ ኤሊን ምን አለቻት?

/ገጽ 5 ላይ ይቀጥላል/

لا تكتب في هذه المنطقة
לא לכתוב באזור זה

לא לכתוב באזור זה
لا تكتب في هذه المنطقة



## ክፍል ሁለት — የሰዋሰው ጥያቄዎች

(20 ነጥብ)

ከ11-18ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ መልስ። ለያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት 4 አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ክበብ።
(እያንዳንዱ ጥያቄ 2.5 ነጥብ አለው፣ በአጠቃላይ 20 ነጥብ።)

## פרק שני – לשון

(20 נקודות)

ענה על כל השאלות 11-18.
בכל שאלה הקף במעגל את האות המסמנת את האפשרות הנכונה, מבין 4 האפשרויות הנתונות.
(לכל תשובה נכונה — 2.5 נקודות; סה"כ — 20 נקודות)

11. እጅግ በጣም ታታሪ ነው፥ __________ አልተሳካለተም።
   (ሀ) ስለዚች
   (ለ) ነገር ግን
   (ሐ) ሰላልሆነ
   (መ) እንኳንስ

12. ባሕሪይዋ ጥሩ ______________ የት በደረሰች ነበር።
   (ሀ) ነገር ግን
   (ለ) አለበለዚያ
   (ሐ) ቢሆን ኖሮ
   (መ) እንዳልሆነ

13. እጅግ በጣም ደካማ ናት፥ ______________ ምግብ በደንብ ስለማትመገብ ነው።
   (ሀ) አለበለዚያ
   (ለ) ምክንያቱም
   (ሐ) እንኳንስ
   (መ) ቢሆን ኖሮ

14. 'ልበ ቢስ' ማለት፦
   (ሀ) የነገሩትን የሚረሳ
   (ለ) ብልጣ ብልጥ
   (ሐ) ታታሪ
   (መ) ጎበዝ

15. 'ለዓይን ያዘ' ማለት፦
   (ሀ) ነጋ
   (ለ) በራ
   (ሐ) መነጽር አደረገ።
   (መ) ጨለመ።

/ገጽ 6 ላይ ይቀጥላል/

16. 'ቀራጥ' የሚለው ቃል ትርጉም፦

(ሀ) በውሳኔው የሚጸና

(ለ) ሰው በመራው የሚሔድ

(ሐ) ፈሪና ሰነፍ

(መ) ቃሉን የማይጠብቅ

17. 'ማቀናጀት' የሚለው ቃል ትርጉም፦

(ሀ) ማለያየት

(ለ) ማዳላት

(ሐ) ማጣመር

(መ) መዘበራረቅ

18. ቅቤ በሙቀት ይቀልጣል ጨው በውሃ ____________፡

(ሀ) ይቀልጣል

(ለ) ይበተናል

(ሐ) ይሟሟል

(መ) ይጋገራል

/ገጽ 7 ላይ ይቀጥላል/

لا تكتب في هذه المنطقة
לא לכתוב באזור זה

לא לכתוב באזור זה
لا تكتب في هذه المنطقة



**פרק שלישי – קטע שלא נלמד**

(25 נקודות)

קרא את הקטע שלפניך, וענה על כל השאלות 27-19 שאחריו רק באמהרית.

**ክፍል ሦስት — ያልተማሩት ምንባብ**

(25 ነጥብ)

ከታች የተሰጠውን ምንባብ ካነበብክ በኋላ ከ19-27 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ።

## ኤይላት

ኤይላት በእስራኤል ውስጥ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ናት። ኤይላት የጥንት ከተማ ስትሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተወሰኑ ጊዜያት ተጠቅሳለች። ኤይላትን የተለያዩ ሕዝቦች ነግሠውባታል።

ኤይላት በእስራኤል ሀገር የደቡብ ክፍል ትገኛለች። ይኸውም በቀይ ባህር ሰሜናዊ ጫፍ ላይ የምትገኝ ከተማ ናት። የኤይላት ከተማ የሕዝብ ብዛት ወደ 50,000 ሲሆን የቆዳ ስፋቷም ወደ 84,789 ዱናም ነው። ከመሃል አገር ጋር የሚያገናኛት መንገድ መኖሩ ለእድገቷ ትልህ አስተዋጽዖ አድርጓል። ኤይላትን ለሕዝበ እስራኤል ልዩ ከሚያደርጋት ነገር አንዱ፥ ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ሲወጡ ካረፉባቸው ቦታዎች አንዷ በመሆኗ ነው። ኤይላትን የተለያዩ ሕዝቦች እንደነገሡባት የተለያዩ የአርኪዮሎጂ ምርምር ግኝቶች ያሳያሉ። በኤይላት ከነገሡት ሕዝቦች፦ ግብጻውያን፣ አዶማውያን፣ ሮማውያን፣ ቱርኮችና እንግሊዞች ይገኙባቸዋል።

በዛሬው ጊዜ ግን ኤይላት በእስራኤል ሀገር ቁጥጥር ሥር ትገኛለች። ኤይላት በእስራኤል ሥር የሆነችው በነጻነቱ ጦርነት ጊዜ ነው። ይኸውም መጋቢት (ማርች) 1949 ዓ.ም. በተደረገው ወታደራዊ ጦርነት ነው። ኤይላት ከመሃል ሀገር ርቃ ብትገኝም በ1975 ዓ.ም. አየር መንገድ ከተሠራባት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የቱሪስት መዳረሻ ሆናለች። ኤይላት ባሕር ዳር ላይ መገኘቷ ለቱሪስት ምቹ አድርጓታል።

/ገጽ 8 ላይ ይቀጥላል/

**ጥያቄዎች**

በምንባቡ መሠረት ከ19-26 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ብቻ መልስ። (እያንዳንዱ ጥያቄ 2.5 ነጥብ አለው። በአጠቃላይ 20 ነጥብ።)

**השאלות**

ענה על שאלות 26-19 באמהרית, לפי הקטע.
(לכל תשובה נכונה — 2.5 נקודות;
סה"כ — 20 נקודות)

19. ኤይላት በየትኛው የእስራኤል ሀገር ክፍል ትገኛለች?

____________________

____________________

20. የኤይላት ከተማ የሕዝብ ብዛት ምን ያህል ነው?

____________________

____________________

21. የኤይላት የቆዳ ስፋት ምን ያህል ነው?

____________________

____________________

22. ለኤይላት እድገት ትልህ አስተዋጽዖ ያደረገው ምንድን ነው?

____________________

____________________

23. ኤይላትን ለሕዝበ እስራኤል ልዩ ከሚያደርጋት ነገር አንዱ ምንድን ነው?

____________________

____________________

/ገጽ 9 ላይ ይቀጥላል/

לא לכתוב באזור זה
لا تكتب في هذه المنطقة

24. የተለያዩ የአርኪዮሎጂ ምርምር ግኝቶች ምንን ያሳያሉ?

25. በኤይላት ከነገሡት ሕዝቦች ቢያንስ ሦስቱን ጻፍ።

26. በ1975 ዓ.ም. በኤይላት ምን ተሠራ?

/ገጽ 10 ላይ ይቀጥላል/

לא לכתוב באזור זה
لا تكتب في هذه المنطقة

በትእዛዙ መሠረት 27ኛውን ጥያቄ መልስ።

ענה על שאלה 30, לפי ההוראות.

27. ከሀ-ሠ ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ካነበብክ በኋላ በምንባቡ መሠረት እያንዳንዱን **እውነት** ወይም **ውሸት** በማለት ትክክለኛውን መልስ ክበብ። (እያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ አንድ ነጥብ አለው፣ በጠቅላላ 5 ነጥብ)

27. בכל אחד מהסעיפים ሀ-ሠ, הקף במעגל את התשובה הנכונה: **נכון** או **לא נכון**, לפי הקטע. (לכל תשובה נכונה — נקודה אחת; סה"כ — 5 נקודות)

ሀ. ኤይላት አዲስ ከተቆረቆሩ ቦታዎች ውስጥ አንዷ ናት። እውነት ውሸት

ለ. ኤይላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሳለች። እውነት ውሸት

ሐ. ኤይላትን ሦስት ሕዝቦች ብቻ ነግሠውባታል። እውነት ውሸት

መ. ኤይላት በቀይ ባህር ሰሜናዊ ጫፍ ላይ የምትገኝ ከተማ ናት። እውነት ውሸት

ሠ. ኤይላት ለመሃል ሀገር ቅርብ የሆነች ከተማ ናት። እውነት ውሸት

/ገጽ 11 ላይ ይቀጥላል/

لا تكتب في هذه المنطقة
לא לכתוב באזור זה

לא לכתוב באזור זה
لا تكتب في هذه المنطقة

## **ክፍል አራት** (25 ነጥብ)

የሚከተለው ምንባብ በክፍል ውስጥ የተማርከው ነው። ምንባቡን ካነበብክ በኋላ ከ28-35 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ <u>ወይም</u> በአማርኛ መልስ።

## פרק רביעי – קטע שנלמד

(25 נקודות)

לפניך קטע.
קרא אותו, וענה על שאלות 28-35 שאחריו בעברית <u>או</u> באמהרית.

### የቀጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

በመንደራችን ውስጥ አንድ ትልቅ፣ አስፈሪ ውሻ ይኖር ነበር። አንድ ቀን በጣም ስለራበው የሚበላ ነገር ፍለጋ ወደ ሌላ መንደር ሄደ። እዛም ሰዎች በሬ አርደው *ሥጋ* ሲከፋፈሉ አየና ከአጠገባቸው ቆመ።

ከሰዎቹም አንዱ ለውሻው አዝኖለት ትንሽ *ሥጋ* ወረወረለት። ውሻውም *ሥጋ*ውን በአፉ ይዞ ወደ ሜካ ሮጠ። ወደሜካውም ሊገባ ሲል ኩሬ (የውሃ ጉድጓድ) አይቶ ቆመ። ወደውሃው ሲመለከትም የራሱን መልክ ከውሃው ውስጥ አየ።

በዚህ ጊዜ ውሻው ሌላ ውሻ በአፉ *ሥጋ* ይዞ የቆመ መሰለው። ስለዚህም የሌላውን ውሻ *ሥጋ* ለመቀማት ፈለገና ለመጮህ አፉን ሲከፍት የያዘው *ሥጋ* አምልጦት ወደ ውሃው ውስጥ ወደቀበት። ከዚያም *ሥጋ*ውን ለማግኘት ቢሞክርም ወደኩሬው ጥልቅ ክፍል ስለሄደበት ሊያገኘው አልቻለም። በዚህም ምክንያት ምንም ሳይበላ በባዶ አንጀቱ ወደቤቱ ሄደ።

/ገጽ 12 ላይ ይቀጥላል/

**ጥያቄዎች** (25 ነጥብ)

በምንባቡ መሠረት ከ28-35 ያሉትን ጥያቄዎች በሙሉ በዕብራይስጥ ወይም በአማርኛ መልስ። (እያንዳንዱ ጥያቄ የያዘው ነጥብ በጥያቄው መጨረሻ ላይ ተጽፏል።)

השאלות (25 נקודות)

ענה על כל השאלות 35-28 בעברית או באמהרית, לפי הקטע.

(מספר הנקודות לכל שאלה רשום בסופה.)

28. በመንደራችን ምን ዓይነት ውሻ ይኖር ነበር?

____________________________________________

(2 ነጥብ)

29. ውሻው ወደ ሌላ መንደር የሄደው ለምንድን ነው?

____________________________________________

(3 ነጥብ)

30. ውሻው ምን ዓይቶ ነው የቀመው?

____________________________________________

(3 ነጥብ)

31. ከሰዎቹ አንዱ ለውሻው አዝኖለት ምን አደረገ?

____________________________________________

(3 ነጥብ)

32. ውሻው ወደ ውሃው ውስጥ ሲመለከት ምን አየ?

____________________________________________

(4 ነጥብ)

/ገጽ 13 ላይ ይቀጥላል/

لا تكتب في هذه المنطقة
לא לכתוב באזור זה

לא לכתוב באזור זה
لا تكتب في هذه المنطقة

33. ውሻው ሥጋው የወደቀበት ምን ሲያደርግ ነው?

(3 ነጥብ)

34. ውሻው የወደቀውን ሥጋ ለማግኘት ሲሞክር ያልተሳካለት ለምንድን ነው?

(4 ነጥብ)

35. ውሻው በምን ሁኔታ ወደቤቱ ሄደ?

(3 ነጥብ)

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך